أحكام الأضحية

የኡዱሕያ ህግጋቶች



تأليف: الشيخ محمد بن صالح العثيمين

ትርጉም ፡ አቡ’ዓብዲልዓዚዝ/ ዩሱፍ አህመድ

ማዉጫ ገፅ

ክፍል አንድ : የሙዱሕያ ምንነትና ሸሪዓዊ ብይኑ 2

ክፍል ሁለት : የኡዱሕያ መስፈርቶች 8

ክፍል ሶስት : ከአይነትና ከባህሪ አኳያ ለኡዱሂያ በላጩ የቱ ነው? የተጠላውስ የቱ ነው? 13

ክፍል አራት : ኡዱሂያ ለማን ነው የሚበቃው? 16

ክፍል አምስት : ኡዱሂያን መለየትና ሸሪዓዊ ብይኑ 18

ክፍል ስድስት : ከኡዱሂያ የሚበላውና ተከፋፍሎ የሚሰጠው 22

ክፍል ሰባት : ኡዱሂያ የሚያርድ ሰው ሊከለከላቸው የሚገቡ ነገሮች 25

ክፍል ስምንት : እርድ እና መስፈርቶቹ 27

ክፍል ዘጠኝ : የእርድ አዳቦች 34

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባው ነው። እናመሰግነዋለን ፤ በእርሱም እንታገዛለን ፤ ይቅርታም እንጠይቀዋለን ፤ ከሓጢያታችን ወደርሱም ተጸጽተን እንመለሳለን። ከነፍሶቻችን ተንኮል ፣ ከተግባሮቻችን ክፋት በአላህ እንጠበቃለን። አላህ የመራውን ማንም አያጠመውም ፤ አላህ ያጠመመውን ደግሞ ማንም አይመራውም።

ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የሌለ መሆኑን ፤ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ደግሞ አገልጋዩና መልእክተኛው መሆናቸውን በእርግጠኝነት እንመሰክራለን።

የአላህ ውዳሴና ሰላምታ በነብዩ ሙሐመድ ﷺ ፣ በቤተሰቦቻቸው ፣ በአጠቃላይ በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የዑለማዎችን ልዩነትና ክርክር ያቀፈ ፣ በኡዱሕያና በእርድ ዙሪያ 93 ገጽ የሚደርስ ኪታብ ጽፌ ነበር። ነገር ግን በውስጥ ያቀፈው መልእክት በዝቶ አሰልች ይሆናል ብየ በመስጋት ፣ አላስፈላጊ የሆነውን በመጣል ፣ አስፈላጊውን በመጨመር እጥር ምጥን አድርጌ እንደሚከተለው ለአንባቢያን አቅርቤዋለሁ።

ይህን ስራየን ለአላህ ብየ የሰራሁት እንዲያደርግልኝ ፤ ሽሪዓውን የሚያብራራና ለእኔም ይሁን ለሙስሊሞች ጠቃሚ እንዲያደርገው አላህን እማጸናለሁ። እንሆ እርሱ ለጋስና ቸር ነውና።

ክፍል አንድ

የዑዱሕያ ምንነትና ሸሪዓዊ ብይኑ

ኡዱሕያ፡ ማለት ወደ አላህ ለመቃረቢያ ተብሎ በኢደል አድሃ ከቤት እንሰሳዎች (ከግመል ፣ ከከብት ፣ ከበግና ከፍየል) የሚታረድ እርድ ነው።

"ኡዱሑያ" ፡ በአላህ ኪታብ ፣ በረሡል ﷺ ሱና እንዲሁም በሙስሊሞች ስምምነት የጸደቀ ከኢስላም ሸሪዓዊ ህግጋት መለያ ምልክቶች መካከል አንዱ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَانْحَرْ﴾

"ስለዚህ ለጌታህ ስገድ ፤ (በስሙ) ሰዋም።) *(አል'ከውሰር፡ 2)*

﴿قُلْ إِنَّ صَلاَتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ۞لاَ شَرِيكَ لَهُ وَبِذَلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَاْ أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ﴾

"ስግደቴ ፣ እርዷ ፣ ሕይዎቴም ፣ ሞቴም ለዓለሚት ጌታ ለአላህ ነው" በል። "ከእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በሚጥራት) ታዘዝኩ ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ" (በል)። *(አል'አንዓም፡ 162-163)*

ሰዒድ ብን ጁበይር - ረሂመሁሏህ - "በዚህ የቁርኣን አንቀጽ ውስጥ "ኑሱክ" በመባል የተጠራው ወደአላህ መቃረቢያ እርድ ወይም አጠቃላይ የአምልኮ አይነቶች የሚል ትርጉም አለው። እርድ የሚለው ትርጉም አምልኮ በሚለው ውስጥ የሚካተት በመሆኑ ሁለተኛው ትርጉም ሁሉን የሰበሰበ ትርጉም በመሆኑ ተመራጭነት አለው" ይላሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلِكُلِّ أُمَّةٍ جَعَلْنَا مَنسَكًا لِيَذْكُرُوا اسْمَ اللَّهِ عَلَى مَا رَزَقَهُم مِّن بَهِيمَةِ الْأَنْعَامِ فَإِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ فَلَهُ أَسْلِمُوا وَبَشِّرِ الْمُخْبِتِينَ﴾

"ከሀዝብም ሁሉ (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን ደነገግን። ከቤት እንስሳት በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ብቻ ያወሱ ዘንድ (አዘዝናቸው)። አምላካችን አንድ አምላክ ነው። ከእርሱም ብቻ ታዘዙ። ከአላህ ተዋራጆችንም አብስራቸው።" *(አል'ሐጅ፡ 34)*

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት አነስ ብን ማሊክ ﷺ የሚከተለውን አስተላልፏል፡-

"ضحى النبي صلى الله عليه وسلم بكبشين أملحين ذبحهما بيده وسمى وكبر ووضع رجله على صفاحهما"

"ነብዩ ﷺ ቢስሚላህ አሏሁ አክበር በማለትና እግራቸውን ከአንገቶቻቸው ላይ በማኖር ሁለት ጥቁር የተቀላቀለባቸው ነጭ በጎችን ከኡዱሕያ በእጃቸው አርደዋል።" *(ቡኻሪ፡ 5565, ሙስሊም፡ 1966)*

وعن عبد الله بن عمر – رضي الله عنهما - قال: "أقام النبي – صلى الله عليه وسلم – بالمدينة عشر سنين يضحي"، رواه أحمد والترمذي وقال: حديث حسن.

ዓብደላ ብን ዑመር ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡-

"ነብዩ ﷺ ኡዱሂያ አያረዱ አስር ዓመት በመዲና ተቀመጥዋል።" *(አህመድ፡ 4955, ቲርሚዚይ፡ 1507)*

ዑቅባ ብን ዓምር ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡-

"የአላህ መልእክተኛ ﷺ ለኡዱሕያ የሚታረዱ እንስሳዎችን አከፋፈሉ። ለዑቅባ

“ጀዘዓህ”[1] ደረሰችው። ከዚያም ዑቅባ “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ለእኔ “ጀዘዓ” ደረሰችኝ” በማለት ረሡልን ﷺ ጠየቃቸው። “አርሲን ከኡዱሁያ አረድ” በማለት ምላሽ ሰጡት። *(ቡኻሪ፡ 5547)*

وعن البراء بن عازب – رضي الله عنه – أن النبي – صلى الله عليه وسلم – قال: "من ذبح بعد الصلاة فقد نسكه وأصاب سنة المسلمين"، رواه البخاري ومسلم.

በራእ ብን ኣዚብ ﷺ የሚከተለውን የረሡል ﷺ ሐዲስ አስተላልፏል፡-

“ከሶላት በኋላ ያረደ ሰው በርግጥ አርዱ ተሟላ ፤ የሙስሊሞችን ሱናም አገኘ።” *(ቡኻሪ፡ 5545, ሙስሊም፡ 1961)*

ረሡልም ﷺ ይሁን ሶሃቦቹ የኡዱሁያ እርድ አርደዋል። ኡዱህያ የሙስሊሞች ሱና መሆኑንም ተናግረዋል። ይህን መሰረት በማድረግ ኡዱህያ ሸሪዓዊ ህግ ለመሆኑ የሙስሊሞች አጠቃላይ ስምምነት እንደሆነ በርካታ ዓሊሞች ግልጽ አድርገዋል። ኡዱሁያ ጠንካራ የሆነ ሱና ነው ወይስ ሊተውት የማይገባ ዋጅብ (ግዴታ) ነው በሚለው ጉዳይ ላይ ብቻ ዑለሞቹ የአመለካከት ልዩነት አምጥተዋል።

አብዛኞቹ ዑለሞች ኡዱሕያ ማረድ ጠንካራ የሆነ ሱና ነው ብለዋል። ይህ ደግሞ የሻፍዒይ ፤ የማሊክ እና የአህመድ ደግሞ በአንደኛው ንግግራቸው መዝሐባቸው መሆኑ ተረጋግጧል። አቡሀኒፋ ፣ ኢማም አህመድ በሌላው ንግግራቸው እና ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያም ዋጅብ (ግዴታ) ነው በሚለው ሐሳብ ላይ ተጉዘዋል። ዋጅብ ነው የሚለው አመለካከት የኢማም ማሊክ ግልጽ የሆነው መዝሀባቸው እንደሆነ ሸይኹል ኢስላም ግልጽ አድርገዋል።

(1). “ጀዘዕ” የሚባለው የአመት ግማሽ የሞላው ነው።

የኡዱሕያ እርድ የነብዩ ﷺ እንዲሁም የሙስሊሞች ተግባር ነው። ምክንያቱም እርድ ከአላህ ዒባዳዎች (አምልኮዎች) መገለጫ መካከል አንዱ ነው። ሰዎች ከኡዱሀያ እርድ ወደሶደቃ (ወደምጽዋት) ቢሸጋገሩ ይህ የሸሪዓ መገለጫ ባዶ ይሆን ነበር። ከኡዱሕያ እርድ ይልቅ በገንዘብ ቢሆን ኖሮ መልካምን ነገር ግልጽ ከማድረግ ወደኋላ የማይሉት ረሡል ﷺ በንግግራቸውም ይሁን በተግባራቸው ያብራሩት ነበር። ኡዱሀያ በማረድና ግምቱን በገንዘብ ማውጣቱ በሸሪዓ እኩል ቢሆን ኖሮ ከኡዱሀያ ይልቅ ኡመታቸው ዘንድ ቀላል የሆነውን የገንዘብ ወጭ ይመርጡላቸው ነበር።

በነብዩ ﷺ ዘመን ሶሃቦች ድርቅ ገጠማቸው ከዚያም የሚከተለውን ተናግሩ፡-

"من ضحى منكم فلا يصبحن بعد ثالثة في بيته شيء"

"ከአናንተ ኡዱሕያ ያረደ ሰው ከሶስት ቀን በኋላ ከቤቱ አንድም ነገር አንዳይኖር።"

መጭው አመት ላይ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ባለፈው አመት እንደሰራነው እንስራ?" በማለት ሶሃቦቹ ጠየቁ። ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡ፡-

"كلوا، وأطعموا، وادخروا، فإن ذلك العام كان في الناس جهد فأردت أن تعينوا فيها" متفق عليه

"በዚያ አመት ላይ በሰዎች ውስጥ ድርቅ ስለነበር ሌላውን አንድታግዙ ለማድረግ ነው ፤ አሁን ግን ብሉ ፣ አብሉ ፣ አከማቹ።" (ቡኻሪ፡ 5569, ሙስሊም፡ 1974)

ኢብን አልቀይም - ረሂመሁሏህ - የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"الذبح في موضعه أفضل من الصدقة بثمنه قال: ولهذا لو تصدق عن دم المتعة والقران بأضعاف أضعاف القيمة لم يقم مقامه وكذلك الأضحية"

"እርድ በተገቢ ቦታው ግምቱን በገንዘብ ከመሰጠት በላጭ ነው። በዚህ ምክንያት ለሙትዓና ለቂራን - የሐጅ ሰርዓቶች - (እርድ በማረድ ምትክ) የተነባበረ የገንዘብ ክፍያ ብትከፍል የእርሱን ቦታ ሊተካ አይችልም። ኡዱሂያም እንዲሁ።"

ከመሰረቱ ኡዱህያ የተደነገገው በህይዎት ለሚገኙ ሰዎች ነው። አንዳንድ ጃሂል የሆኑ ሰዎች ኡዱሁያን ለሚቾች ነይተው እንደሚያርዱት ሳይሆን ረሡል ﷺ ይሁኑ ሶሃቦች ለራሳቸውም ይሁን በህይዎት ለሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ኡዱሁያን ያርዱ ነበር።

አንድ ሰው ለሙታን ኡዱህያ አርዳለሁ ካለ ከሚከተሉት ሶስት ዓይነት ክፍሎች ውጭ ሊሆን አይችልም።

የመጀመሪያው፡- ኡዱህያ ሲያርድ መጀመሪያ በህይዎት ያሉትን ሰዎች ነይቶ በተከታይነት በኡዱህያው ምንዳ ተካፋይ እንዲሆኑ የሞቱትን ሰዎች ማካተት ይችላል። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ለራሴም ፣ በህይዎት ላሉትም ቤተሰቼ እንዲሁም በህይዎት ለሌሉት ብሎ በመነያት ኡዱሁያውን ማረድ ይችላል። የዚህ መሰረቱ የነብዩ ﷺ እርድ ነው። ስለራሳቸው ፣ ስለቤተሰባቸው ፣ ከእነርሱ መካከል ከዚህ በፊት ስለሞቱትም ነይተው አርደዋል።

ሁለተኛው፡- ሚቾች ከተናዘዙ በኑዛዜው መሰረት ተፈጻሚ የሚሆን ኡዱህያ ነው። ለዚህ መሰረቱ የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿فَمَن بَدَّلَهُ بَعْدَ مَا سَمِعَهُ فَإِنَّمَا إِثْمُهُ عَلَى الَّذِينَ يُبَدِّلُونَهُ إِنَّ اللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ﴾

"(ኑዛዜውን) ከሰሚውም በኋላ የከወጠው ሰው ሃጢያቱ በነዚያ በሚከውጡት ካይ ብቻ ነው። አላህ ሰሚ ዐዋቂ ነውና።" *(አል'በቀራህ፡ 181)*

ሶስተኛው፡- በህይዎት ያሉ ሰዎች ስለሙታኖች በበጎ ውለታ ራሱን አስችለው ነይተው የሚያርዱት ነው። ይህ አይነቱ ለሟቾች የሚደረገው በጎ አድራጎት ይበቃል እንላለን። የሀንበልያ ፉቀሀዎች በሶደቃ ቀይሰው ምንዳው ወደሟቹ እንደሚደርስና ተጠቃሚ እንደሚሆን በግልጽ አስቀምጠዋል። ነገር ግን ይበቃል ብንልም ሙታንን በኡዱህያ መለየቱ ሱና ነው የሚል አመለካከት የለንም። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ በተለየ ሁኔታ ለሙታኖች ኡዱህያን አላረዱም። ከእርሳቸው ዘንድ በጣም ተወዳጅና የተላቀ ስለሆነው አጎታቸው ሀምዛ አላረዱም። በህይዎት እያሉ ስለሞቱት ወንድ ልጆቻቸውም አላረዱም። ከርሳቸው ዘንድ በጣም ተወዳጇ ስለሆነችው ሚስታቸው ኸዲጃም አላረዱም። በዘመናቸው የነበሩትም ሶሃቦች ለሞቱ ዘመዶቻቸው እንዳረዱ የሚገልጽ መረጃ እስካሁን አልተገኘም።

አንዳንድ ሰዎች ለሞተባቸው ዘመዶቻቸው በሞቱ በአመቱ (ኡዱህያ አልሀፍራ) በሚል ስያሜ እርድ ያርዳሉ። በዚህ እርድ ላይ በምንዳ አንድም ሰው አይጋራውም ብለው ያምናሉ። ይህ ተግባራቸው በጣም ስህተት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ቢያውቅ እና ቢገነዘብ ኖሮ ኡዱህያ በሚያርድበት ጊዜ በነብዩ ﷺ ሱና መሰረት ለራሱ ፣ ለቤተሰቦቹ በህይዎት ይኑሩም አይኑሩ በመነያት ማረድ ይችል ነበር። ሱና ወዳልሆነ ተግባርም ባልተዘነበሉ ነበር።

ክፍል ሁለት

የኡዱሕያ መስፈርቶች

ለኡዱሀያ ስድስት መስፈርቶች አሉት፡

አንደኛ፡- የሚታረዱት ከቤት እንሰሳዎች መካከል መሆን አለበት። እነርሱም ግመል ፣ ከብት ፣ ፍየልና በግ ናቸው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلِكُلِّ أُمَّةٍ جَعَلْنَا مَنسَكًا لِيَذْكُرُوا اسْمَ اللَّهِ عَلَى مَا رَزَقَهُم مِّن بَهِيمَةِ الْأَنْعَامِ﴾

"ከሕዝብም ሁሉ (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን ደነገግን። ከቤት እንሰሳት በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ብቻ ያወሱ ዘንድ (አዘዝናቸው)።" *(ሐል'ሐጅ፡ 34)*

ሀሰን ፣ ቀታዳ እና ሌሎችም "የቤት እንስሳት ማለት ግመል ፣ ከብት ፣ ፍይልና በግ በመሆናቸው ከዓረቦች የሚታወቅ ነው" ብለዋል።

ሁለተኛው፡- በሸሪዓ በተደነገገው የእድሜ መጠን መሆን አለበት። ከበግ "ጀዘዕ" ፣ ከበግ ውጭ ከሆነ ደግሞ "ሰንያ" መሆን አለባት።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"لا تذبحوا إلا مسنة إلا أن تعسر عليكم فتذبحوا جذعة من الضأن"

"በእናንተ ላይ ችግር እስካልሆነ ድረስ ሙሲናን እንጅ አትረዱ ከበግ ጀዘአ እረዱ።" *(ሙስሊም፡ 1963)*

"ሙሲና" የምትባለው ሰንያና ከእርሷ በላይ የሆነችው ነች። "ጀዘዓ" ደግሞ ከእርሷ

በታች የሆነችው ነች። ከግመል "ሰንይ" የሚባለው ፡ አምስት አመት የሞላው ነው። ከከብት ደግሞ "ሰንይ" የሚባለው ሁለት አመት የሞላው ነው። ከፍየል "ሰንይ" የሚባለው አመት የሞላው ነው። "ጀዘዕ" የሚባለው የአመት ግማሽ (6 ወር) የሆነው ነው። ከግመል ፣ ከከብት ፣ ከፍየል ከሰንይ በታች ኡዱሂያ አይታረድም። ከበግም ከጀዘእ በታች አይታረድም።

ሶስተኛው፡- ከመብቃት የሚከለክሉ ነውሮች የጸዳ መሆን አለበት። እነርሱም አራት ናቸው።

1. **ግልጽ የሆነ አንድ አይና፡-** አይኑ የተሰረጎደ ወይም በይፋ ነጩ ክፍል ወጥ አንድ አይና መሆኑን የሚጠቁም፤
2. **ግልጽ የሆነ በሽታ፡-** በእንስሳው ላይ በሽታው በግልጽ የሚታወቅ ። እሳር ከመጋጥ ፣ የመመገብ ፍላጎቷን የሚከለክል የሚያንቀጠቅጥ በሽታ በይፋ መታየቱ ነው። ለስጋዋ ወይም ለጤናዋ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር ግልጽ የሆነ የቆዳ በሽታ ወይም ቁስለት ሊኖርባት ነው።
3. **ግልጽ የሆነ አንካሳነት፡-** በሰላም እንዳትሄድ የሚያደርጋት የእግር አንካሳነት ነው።
4. **ስብና ቅባትን ባዶ የሚያስቀር መክሳት፡** ማሊክ ሙወጦእ ላይ በዘገቡት በራእ ብን ዓዚብ ﷺ ባስተላለፈው ሐዲስ ረሡል ﷺ ከኡዱሂያ ልንጠነቀቀው የሚገባ ምንድን ነው? ተብለው ተጠይቀው ነበር። በእጃቸው ጠቆሙ ፡ "አራት ነገሮች ናቸው፡ ሸባነቷ ግልጽ የሆነ ፣ አንድ ዓይና መሆኗ ግልጽ የሆነ ፣ በሽታዋ ግልጽ የሆነ ፣ ስብ የለላት ከሳዋ" በማለት ምላሽ ሰጠዋል።

በሱነን ደግሞ የአላህ መልእክተኛ ﷺ በመካከላችን ቆመው የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"አራት አይነቶች ከኡዱሐያ አይበቁም ..." (አቡዳውድ፡ 2802, ቲርሚዚይ፡ 1497, ነሳኢይ፡ 4369)

እነዚህን አራት ነውሮች የመሰሉ ወይም ከእነርሱም የከፉ ሆነው ወደነዚህ አራት ነውሮች የሚጠጉ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡ -

- በሁለት አይኖቿ የማትመለከት
- ቁንጣን በሽታ ያለባት
- ምጡ ጠንቶባት በመውለድ ላይ ያለች
- በመታነቅ ወይም ከከፍታ ቦታ ተንከባላ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባት
- ለመሄድ ያቃታት ደካማ
- ሁለት እጆቿ ወይም ሁለት እግሮቿ የተቆረጡ

አራቱ ነውሮችና እነዚህን ስድስት ነውሮች ስንደምራቸው ለኡዱሀያ የማይበቁ በጥቅሉ አስር ይሆናሉ ማለት ነው።

አራተኛው፡ - ኡዱሁያዋ የሚያርደው ሰው ንብረት መሆን አለባት። የእርሱ ንብረት ያልሆነን ለኡዱሕያ ማቅረብ የተከለከለ ነው። ለምሳሌ፡ ዘርፎ ወይም ሰርቆ ወይም በሀሰት እና በቅጥፈት ያመጣውን እንስሳት አርዶ ወደአላህ መቃረቢያ ማድረግ ክልክል ነው።

አምስተኛ፡ - ከሌላ ሀቅ ጋር የተያያዘ መሆን የለበትም። ለምሳሌ፡ - በዋስትና የተያዘችን እንስሳት ለኡዱሀያ ማቅረብ ክልክል ነው።

ስድስተኛ፡ - ኡዱሕያው በሸሪዓ በተደነገገው ወቅት ወይም ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት። የሚታረድበት ቀን ከየውመ ነሕር (ዙልሂጃ አስረኛው ቀን) ጀምሮ ዙልሂጃ አስራ ሶስተኛው ወይም አያመተሽሪቅ መጨረሻው ቀን ጸሀይ እስክትጠልቅ ድረስ ማረድ ይችላል።

ዒድ ሶላት ከማብቃቱ በፊት ወይም አያመ ተሸሪቅ ዙል ሂጃ አስራሶስተኛው ቀን ጸሀይ ከጠለቀች በኋላ ኡዱሁያ ያረደ ሰው እርዱ ተቀባይነት የለውም።

ማስረጃችን የሚከተለው የረሱሠል ﷺ ሐዲስ ነው፡-

أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "من ذبح قبل الصلاة فإنما هو لحم قدمه لأهله وليس من النسك في شيء"

"ከሶላት በፊት ያረደ ሰው ለቤተሰቦቹ ያስቀደመው ስጋ እንጅ ከኡዱሀያው አንዳችም ነገር የለው።" *(ቡኻሪ፡ 5545, ሙስሊም፡ 1961)*

ጁንዱብ ብን ሱፍያን አልበጀልይ ﷺ የሚከተለውን የረሠል ﷺ ሐዲስ አስተላልፏል፡-

"من ذبح قبل أن يصلي فليعد مكانها أخرى"

"(የዒድ ሶላት) ከመሰገዱ በፊት ያረደ በእርሷ ቦታ ሌላ ይተካ" *(ቡኻሪ፡ 5562, ሙስሊም፡ 1960)*

ነቢሻ አልሁዘልይ ﷺ ደግሞ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡-

"أيام التشريق أيام أكل وشرب وذكر لله عز وجل"

"አያመ ተሸሪቅ የምግብ ፣ የመጠጥ እና አላህን የመዝከሪያ ቀን ነው።" *(ሙስሊም፡ 1141)*

ሸሪዓዊ በሆነ ምክንያት የኡዱሁያን እርድ ከአያመ ተሸሪቅ ቢያዘገየው ለምሳሌ - ከእርሱ ምንም አይነት ጉድለት ሳይኖር ለኡዱሀያ የገዛት በግ ብትጠፋና ወቅቱ ከወጣ በኋላ ብትገኝ ወይም ኡዱሁያ እንዲያርድለት የወከለው ሰው ቢረሳና ወቅቱ ከወጣ በኋላ ኡዱሁያው ቢታረድ ችግር የለውም። ይህ ሸሪዓዊ ብይን በእንቅልፍ ምክንያት ወይም በመርሳት ሶላቱን ያሳለፈ ሰው ትዝ እንዳለው ወይም ከእንቅልፉ እንደነቃ ይስገደው በሚለው ሸሪዓዊ ብይን ተቀይሶ (ተነፃፅሮ) ነው።

የኡዱህያን እርድ በሌሊትም ይሁን በቀን ማረድ ይቻላል። በቀን ማረዱ ደግሞ በላጭነት አለው። በተለይም የዒድ ቀን ከኹጥባ በኋላ በቀጥታ ማረዱ ደግሞ ከሁሉም በላጭ ነው።

ክፍል ሶስት

ከእይነትና ከባህሪ አኳያ ለኡዱህያ በላጩ የቱ ነው? የተጠላውስ የቱ ነው?

ከእይነት ለኡዱህያ በላጭ የሚሆነው ብቻውን ሆኖ ሙሉ የሚያርድ ከሆነ ቁጥር አንድ ግመል በመቀጠልም ከብት ከዚያም በግ በመቀጠል ፍየል ነው። ለሰባት (ከዛ በታች ሆነው) የሚካፈሉ ከሆነ ደግሞ ቁጥር አንድ ግመል ከዚያም ከብት ነው።

ከባህሪ አንጻር በላጭ የሚሆነው ስጋ ብዛት ያላትና የሰባች ፣ አፈጣጠሯ ሙሉ የሆነ እና ሲመለከቷት የምታምረዋ ነች።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ጥቁር የተቀላቀለባቸው ሁለት ነጭ ቀንዳማ በጎችን እንዳረዱ ቡኻሪ ሰነድ ላይ አነስ ብን ማሊክ ﷺ አስተላልፏል። *(ቡኻሪ፡ 5558, ሙስሊም፡ 1966)*

አቡሰዒድ አልኹድርይ ﷺ ደግሞ የሚከተለውን አስተላልፏል -

"ነብዩ ﷺ በጥቁር የሚበላ ፣ በጥቁር የሚመለከት ፣ በጥቁር የሚራመድ ቀንዳማ የሆነ ወጠጤ በግ ለኡዱህያ አረዱ።" *(አቡዳውድ፡ 2796, ቲርሚዚይ፡ 1496, ነሳኢይ፡ 4390, ኢብኑ ማጀህ፡ 3128)*

(በጥቁር ይበላል ፤ በጥቁር ይመለከታል ፤ በጥቁር ይሄዳል) ማለት አፉ እና እግሮቹ እንዲሁም አይኖቹ ዙሪያ ላይ ጥቁር ቀለም ያለበት በግ ማለት ነው።

አቡራፊዕ የተባለው የነብዩ ﷺ ባሪያ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

"كان النبي صلى الله عليه وسلم إذا ضحى اشترى كبشين سمينين"

"ነብዩ ﷺ ኡዱሀያ ማረድ (ባሰቡ) ጊዜ ሁለት የሰቡ በጎችን ይገዙ ነበር።" *(አህመድ፡ 27190)*

በሌላ ቃል ደግሞ “መውጁዓይኒ” (ሁለት ቅጥቅጥ የሆኑ በጎችን ይገዙ ነበር) የሚል ኢማም አህመድ ዘግበዋል።

“ሰሚን” ማለት ስጋውና ስቡ የበዛ ማለት ነው። “መውጁዕ” ማለት ደግሞ ቅጥቅጥ ማለት ነው። ከስጋ ማማር አኳያ በአብዛኛው ከወጠጤው ቅጥቅጡ የተሻለ ይሆናል። ከሰውነት አካልና ከአፈጣጠር አኳያ ደግሞ ወጠጤው ከቅጥቅጡ የተሻለ ይሆናል።

ለኡዱሕያ የተጠሉ የሆኑ የእንስሳት አይነቶች፦

1. “አድባእ” ፡ ጀሮው ወይም ቀንዱ እስከግማሽ ወይም ከዚያ በላይ የተቆረጠ፤
2. “ሙቃበላ” ፡ ከፊት ለፊት በኩል ጀሮዋ በአግድመት የተቀደደ፤
3. “ሙዳበራ” ፡ ከኋላ በኩል በአግድመት ጀሮዋ የተቀደደ፤
4. “አሽ'ሸርቃእ” ፡ በርዝመት ጀሮዋ የተቀደደ፤
5. “አል'ኻርቃእ” ፡ ጀሮዋ በርካታ ቦታዎች ላይ የተቀዳደደ
6. “አል'ሙስፊራ” ፡ የጀሮው የውስጡ ክፍል መቀደድ፤
7. “አል'ሙስተእሶል” ፡ ቀንዷ ሁሉም የተወገደ፤
8. “አል'በኽቃእ” ፡ አይኑ እንዳለ ሆኖ እይታው የተወገደ፤
9. “አል'መሽዓህ” ፡ በሀይል እየተነዳች ካልሆነ በቀር ከጓደኞቿ በራሷ አቅም መድረስ የማትችል፤

እዚህን ነውር ያለባቸውን እንስሳዎች መራቁ የተሻለ ነው።

ከላይ ወደጠቀስናቸው የሚጠጉ ተመሳሳይ እንስሳዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፦

1. ከግመል ፣ ከከብት ፣ ከፍየል የጅራቷ ግማሽ ወይም ከዚያ በላይ የተቆረጠ፤
2. ላቱ ከግማሽ ያነሰ መቆረጥ። ከግማሽ በላይ ከተቆረጠ አብዛኛው ዑለማ ለኡዱሀያ

አይበቃም ብለዋል። በተፈጥሮው ላቱን ሙሉውን ያጣ ችግር የለውም።

3 . ብልቱ የተቆረጠ፤

4 . የተወሰኑ የጥርስ ክፍሎቹ መውለቅ። በተፈጥሮው የወለቀ ከሆነ የተጠላ አይደለም።

5 . ከጡቷ ክፍል የተወሰነው መቆረጥ። በተፈጥሮ የተቆረጠ ከሆነ ችግር የለውም።

ሁለቱን ስንደምረው አስራ አራቱ አይነቶች የተጠሉ ናቸው።

ክፍል አራት

ኡዱህያ ለማን ነው የሚበቃው?

አንድ ኡዱሁያ ለግለሰቡ ፣ ለቤተሰቦች እና ለፈለገው ሙስሊም ማረድ ይበቃል።

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ዓኢሻ ﵂ ያስተላለፈችው ሐዲስ ነው። ነብዩ ﷺ እግሩ ጥቁር ፣ ጉልበቱ ጥቁር ፣ አይኑ አካባቢ ጥቁር የሆነ በግ መጣላቸው ከዚያም "ዓኢሻ ሆይ! ቢካዋውን አቅርቢልኝ" አሏት እርሷም አቀረበችላቸው። በጉን አጋድመው ከያዙ በኋላ "ቢስሚካህ ፣ አኪሁመ ተቀበል ሚን ሙሀመዲን ወአሂ ሙሀመዲን ወሚን ኡመቲ ሙሀመዲን" በማለት አረዱት። *(ሙስሊም፡ 1967)*

አቡራፊዕ ﵁ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"ነብዩ ﷺ ሁለት በጎችን ለኡዱህያ ያርዱ ነበር። አንድኛውን ለእርሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው፤ ሁለተኛውን ደግሞ ለአጠቃላይ ኡመቱ" *ሐዲሱን ኢማም አህመድ ዘግበውታል*

አቡአዩብ አልአንሷርይ ﵁ የሚከተለውን ተናገሩ፡-

"በረሡል ﷺ ዘመን አንድ ሰው ለእርሱና ለቤተሰቦቹ ኡዱህያ ካረደ በኋላ ይበሉም ፣ ያበላሉም ነበር።" *(ቲርሚዚይ፡ 1505, ኢብኑ ማጀህ፡ 3147)*

አንድ ሰው በአንድ ኡዱህያ እርሱ ለነያው ሁሉ ሰው ያብቃቃል። ለራሱ ፣ ለቤተሰቡ እና በህይዎት ይኑርም ይሙትም ለሚፈልገው ሙስሊም ሁሉ ማድረግ ይችላል። አንድ ሰው እከሌ ብሎ ሳይለይ በጥቅል በግ ወይም ፍየል ኡዱህያ ቢያርድ በቋንቋም ይሁን በልምድ ቤተሰቦቹ ሁሉ ይካተታሉ። በልምድ ከሄድን ሚስቶቹ ፣ ልጆች ቅርብ ዘመዶቹ ሁሉ ይካተታሉ።

በቋንቋ ከሄድን ደግሞ ማንኛውም የአባት ዘመድ ፣ የእያቱ ዘመድ ፣ የእያቱ አባት ዘመድ ሁሉ ይገባሉ።

ከፍየል ወይም ከበግ አንዷ ብቻ እንደምታብቃቃው ከከብት ወይም ከግመል ደግሞ አንድ ሰባተኛው ያብቃቃል። አንድ ሰው የአንድ ከብት አንድ ሰባተኛውን ቢካፈል ለርሱም ይሁን ለቤተቦቹ ሁሉ ያብቃቃል። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ የግመል ፣ የከብት አንድ ሰባተኛው የፍየል ወይም የበግን ቦታ እንደሚተካ ተናግረዋል። ለሀድይ - በሐጅ ጊዜ የሚታረድ - የሆነው ሁሉ ለኡዱሁያም ይሆናል። ምክንያቱም በእርሱ እና በሀድይ መካከል ልዩነት ስለሌለ።

ልክ በግመልና በከብት ለሰባት ተጋርተው ኡዱሀያ እንደሚያርዱት አንድ በግ ገዝተው ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ በጋራ ኡዱሀያ ማረድ አይችሉም። ምክንያቱም ምንም አይነት የቁርአንም ይሁን የሀዲስ ማስረጃ ስላልመጣ። ምክንያቱም ዒባዳ ተውቂፍይ ነው (ከአላህ ወይም ከረሡል ﷺ በመጣው ብቻ የተገደበ ነው)። በቁጥርም ይሁን በአይነት ድንበር ማለፍ ተገቢ አይደለም። በምንዳ መጋራት በሸሪዓ የተገኘ ጉዳይ ነው።

ክፍል አምስት

ኡዱህያን መለየትና ሸሪዓዊ ብይኑ

ከሁለት መንገዶች በአንዱ ኡዱህያን መለየት ይቻላል።

አንደኛው፡- በቃል መለየት ፡ ይህች ለኡዱህያ የማርዳት ነች ብሎ መለየቱ ነው።

ሁለተኛው፡- በተግባር መለየት ፡ ይህ ሁለት አይነት ነው።

1. በኡዱህያ ኒያ ማረዱ ነው። በዚህ ኒያ እስካረዳት ድረስ የኡዱህያ ሁክም ተረጋገጠ ማለት ነው።
2. በኡዱህያ ኒያ መግዛቱ ነው። የገዛት የኡዱያ በግ በራሱ ችግር ብትጠፋ እና በእርሷ ምትክ ሌላ ቢገዛ በመግዛቱ ብቻ ለኡዱህያ ነይቶታል ማለት ነው። ምክንያቱም ለጠፋችው ትክ ታሳቢ አድርጎ ነው የገዛት። የተተካው የተተኪውን ሸሪዓዊ ብይን ይይዛል።

እንስሳቷ ለኡዱህያ ተብላ ከተለየች ከእርሷ ጋር የተያያዙ ሸሪዓዊ ብይኖች ምንድን ናቸው?

አንደኛ፡- ከኡዱህያው ጥቅም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ካልሆነ በቀር ኡዱህያን የሚከለክሉ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የተከለከለ ነው። ለምሳሌ፡ መሸጥ ፣ ስጦታ ማድረግ ፣ ለመያዣነት ማዋል እና የመሳሰለውን ተግባር ከመፈጸም መቆጠብ። ለኡዱህያ ብሎ አንድ ፍየል ገዛ ፣ ከዚያም ነፍሱ በጣም ተደሰተችና ይህችን ለርቢ ማቆየት አለብኝ ብሎ ከነበረችው በተሻለ ቀየረ ይህ ለአላህ ብሎ ከነየተው በኋላ መመለስ በመሆኑ ለእርሱ አይበቃም።

ሁለተኛ፡- ለኡዱሀያ ብሎ ከነያና ከለያት በኋላ ቢሞት ወራሾች የግድ መፈጸም ይኖርባቸዋል። ለኡዱሀያ ብሎ ከመነየቱና ከመለየቱ በፊት ከሞተ ግን የእነርሱ ንብረት ናት ለፈለጉት አላማ ማዋል ይችላሉ።

ሶስተኛ፡- ከእርሷ ጥቅሞች በአንዳች ነገር ላይ ተጠቃሚ መሆን የለበትም። ለምሳሌ፡ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ካልኖረና በእርሷ ላይ ጉዳት የማያመጣ ካልሆነ በቀር ለኡዱሀያ የነያትን ለእርሻ ፣ ለመጋለብና ለመሳሰሉ አገልግሎቶች ማዋል የለበትም። የእርሷን አካል በሚቀንስ ሁኔታ ወተት ማለብ የለበትም። ለእርሷ የሚጠቅም ካልሆነ በቀር ወይም በእርሱ ሶደቃ ሊሰጥ ፣ ወይም ስጦታ ሊሰጥ ወይም ሳይሸጥ እርሱ ሊጠቀምበት ካልሆነ በቀር ከጸጉሯና ከመሳሰሉ የአካል ክፍሎች ቆርጦ መውሰድ የለበትም።

አራተኛው፡- ለኡዱሀያ ከሚያበቃው መስፈርት የሚያጎድል የሆነ ነውር ተገኝባት። ለምሳሌ፡ ፍየል ከገዛ በኋላ አንድ አይኗ በግልጽ የታወረ መሆኑ ግልጽ ሆነ። በዚህ ጊዜ ሁሉት አማራጮች አሉ፡

- ይህ ክስተት የተፈጠረው በእርሱ ጉድለት ከሆነ ከበፊቷ የተሻለች ሌላ ገዝቶ ይተካ። ነውር ያለባትን ለእርሱ ንብረት በማድረግ ለፈለገው አገልግሎት ማዋል ይችላል።
- ከእርሱ ምንም አይነት ጥፋት ከሌለ ግን ነውረኛም ብትሆን ለኡዱሀያ አገልግሎት ያውላት።

አምስተኛው፡- ለኡዱሀያ የገዛት እንስሳት ከጠፋች ወይም ከተሰረቀች ሁለት ባህሪ አላት

- ከራሱ ጉድለት ከሆነ ለምሳሌ፡- ጥንቃቄ በሌለበት ቦታ እኑሯት ብታመልጥ ወይም ብትሰረቅ በእርሷ ተመሳሳዩዋን ወይም የተሻለችውን የመተካት ግዴታ አለበት። የጠፋችው ወይም የተሰረቀችው ብትገኝ ለፈለገው ጥቅም ማዋል ይችላል።
- ከእርሱ ምንም አይነት ጉድለት ሳይገኝ ብትጠፋ ወይም ብትሰረቅ የመተካት ግዴታ የለበትም። ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ቢያገኛት የእርድ ወቅቱ ቢያልፍ እንኳ ኡዱሁያውን ታሳቢ አድርጎ ይረዳት።

ስድስተኛው፡- የኡዱሁያ እንስሳት ብትሞት ሶስት ዓይነት ባህሪዎች አሏት፡-

1. ከሰው ልጅ ስራ ውጭ ብትጠፋ፡ ለምሳሌ፡ በበሽታ ወይም በሰማይ መብረቅ ብትሞት የመተካት ግዴታ የለበትም።
2. ለእርሷ መሞት ምክንያቱ ባለቤቷ ቢሆን ተመሳሳይ ወይም ከእርሷ የተሻለችውን ገዝቶ ማረድ አለበት።
3. ከባለቤቱ ውጭ በሌላ አካል ብትጠፋ ለምሳሌ ሽፍታ ቢወስዳት ሸሪዓዊ ብይኑ ልክ እንደመጀመሪያው ነው። የሰረቃት አካል ቢገኝና ካሳውን የሚከፍል ከሆነ ባለቤቱ ተመሳሳዩዋን ገዝቶ ኡዱሀያ ማረድ አለበት።

ሰባተኛው፡- በኡዱሀያ ኒያ ከእርድ ወቅት በፊት ብትታረድ ሸሪዓዊ ብይኑ ከዚህ በፊት እንዳሳለፍነው ነው። በእርድ ወቅት ብትታረድ አራጁ ባለቤቱም ይሁን የተወከለው አካል ትክክለኛ ቦታዋን አግኝታለች ማለት ነው። አራጁ ከባለቤቱም ይሁን ከወኪሉ ውጭ ከሆነ ሶስት ባህሪዎች አሉት፡-

1. ስለባለቤቱ ነይቶ አርዶ ከሆነ እና ባለቤቱ ወዶ ከተቀበለ ታብቃቃለች። ካልወደደ ግን በትክክለኛው የዑለማ አመለካከት አታብቃቃም። ባለቤቱ ይቅር እስካላለ ድረስ አራጁ ተመሳሳዩዋን ገዝቶ ለባለቤቱ ማቅረብ አለበት።

2. በኢማም አህመድ በሻፍዕይ በአቡሀኒፋ የታወቀው አመለካከት ደግሞ ባለቤቱ ባይወድም ለኡዱህያ ያብቃቃለታል የሚል ነው።

3. የእርሱ አለመሆኗን እያወቀ የሌላ ሰው ኡዱሁያ በእርሱ ስም ነይቶ አረደ። ለእርሱም ይሁን ለሌላ አታብቃቃም። ይህ ሰው ባለቤቱ ይቅር እስካላለው ድረስ አምሳያዋን ገዝቶ ለባለቤቱ መስጠት ግዴታ አለበት።

4. ለአንድም ሰው ሳይነያ ቢያርደው ለማንም ኡዱሁያው አያብቃቃም። አንዳንድ ዑለሞች ለባለቤቱ ያብቃቃል ብለዋል።

ክፍል ስድስት

ከኡዱህያ የሚበላውና ተከፋፍሎ የሚሰጠው

ለኡዱህያው ባለቤት ከኡዱህያው መብላት ፣ ስጦታ መስጠትና መሶደቅ በሸሪዓ ተደንግጓል።

አላህ በተከበረው ቀርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَكُلُوا مِنْهَا وَأَطْعِمُوا الْبَائِسَ الْفَقِيرَ﴾

"ከእርሷም ብሉ ። ችግረኛ ድሃንም አብሉ።" *(አል'ሐጅ፡ 28)*

﴿فَكُلُوا مِنْهَا وَأَطْعِمُوا الْقَانِعَ وَالْمُعْتَرَّ﴾

"ከእርሷ ብሉ ከሚኝንም ከልመና የሚያገዳድምን አብሉ።" *(አል'ሐጅ፡ 36)*

ከሰለማ ብን አክወዕ ﷺ የሚከተለው ሀዲስ ተላልፏል፡-

"كلوا، وأطعموا، وادخروا" رواه البخاري

"ብሉ ፣ አብሉ ፣ አከማቹ" *(ቡኻሪ፡ 5569)*

ማብላት ሲባል ለሀብታሞች ስጦታን ፣ ለደሃዎች ደግሞ ሶደቃን የሚያካትት ነው።

ከዓኢሻ ﷺ የተላለፈው ሐዲስ የሚከተለው ነው፡-

"كلوا، وادخروا، وتصدقوا" رواه مسلم

"ብሉ ፣ አከማቹ ፣ (ለምስኪኖች) ሶድቁ" *(ሙስሊም፡ 1971)*

የሚበላው ፣ ስጦታ የሚሰጠው እና ሶደቃ የሚሶደቀውን መጠን በተመለከተ ዑለሞች የተለያየ አመለካከት አንጸባርቀዋል። ተመራጩ አንድ ሶስተኛውን መብላት ፣ አንድ ሶስተኛውን ስጦታ መስጠት ፣ አንድ ሶስተኛውን ደግሞ ለምስኪኖች መሶደቅ ነው።

ምግቡ በመቆየቱ የሚያደርሰው ጉዳት እስከሌለ ወይም የድርቅ ወራት እስካልሆነ ድረስ መከዘንም ተፈቅዷል። የድርቅ ወራት ከሆነ ከሶስት ቀን በላይ መከዘን አይፈቀድም።

ለዚህ መረጃ የሚሆነው **ሰለማ ብን አል'አክወዕ** ﷺ ያስተላለፈው ሐዲስ ነው፡-

"من ضحى منكم فلا يصبحن بعد ثالث وفي بيته منه شيء"

"ከአናንተ አዱሀያን ያረደ ሰው ፣ በቤቱ የሆነ ነገር አያክ ከሶስት ቀን በላይ አንዳያድር ።"

በሚቀጥለው አመት ላይ *"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ባለፈው አመት እንደሰራነው እንሰራ?"* በማለት ሶሃቦቹ ጠየቁ። የአላህ መልእክተኛም የሚከተለውን ምላሽ ሰጡ፡-

"كلوا وأطعموا وادخروا فإن ذلك العام كان في الناس جهد فأردت أن تعينوا فيها"

"በዚያ አመት ላይ በሰዎች ውስጥ ድርቅ ስለነበር ኬላውን አንድታግዙ ለማድረግ ነው ፤ አሁን ግን ብሉ ፣ አብሉ ፣ አከማቹ።" *(ቡኻሪ፡ 5569)*

ኡዱህያ ላይ ዋጅብም ይሁን ትርፍ በመብላቱና በመስጠቱ ዙሪያ በሂዎት ላለም ይሁን ለሞተ ፣ የኑዛዜም ይሁን ሸሪዓዊ ብይኑ እኩል ነው። ኑዛዜ የተደረገለት አካል በተናዛዡ ቦታ ይተካል። እርሱም ከኡዱህያው ይበላል ፣ ስጦታም ይሰጣል። የተወከለ ሰው ከሆነ ደግሞ የወከለው አካል እንዲበላ ፣ ስጦታ እንዲሰጥ ከፈቀደ ወይም አመላካች ሁኔታዎች የሚያስረዱ ከሆነ ተፈጻሚ ይሆናል። ካልሆነ ግን ለወከለው አካል ይሰጣል የማከፋፈሉን ስራ ባለቤቱ ተፈጻሚ ያደርጋል።

ከኡዱህያው አካል ስጋም ይሁን ቆዳ መሸጥ ፣ ለአራጁ እንደዋጋ መክፈል የተከለከለ ነው። ሶደቃ የተሰጠው አካል የተሰጠውን ነገር በፈለገው አይነት ማዋል ይችላል። ከሰጠው አካል ውጭ ለሌላ አካል የመሸጥ መብት አለው።

ክፍል ሰባት

ኡዱህያ የሚያርድ ሰው ሊከለከላቸው የሚገቡ ነገሮች

አንድ ሰው ኡዱህያ ለማረድ ካሰበ ጨረቃን በመመልከትም ይሁን የዙልቃእዳን ወር ሰላሳ ቀን በመሙላት የዙል ሂጃን ወር አንድ ብሎ ከገባ ጀምሮ ኡዱህያውን እስኪያርድ ድረስ ከጸጉሩም ይሁን ከጥፍሩ መቁረጥ ሀራም ሆኖበታል።

ለዚህ ማስረጃችን የኡሙሰለማ ﵂ ሐዲስ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናገሩ፡- **"የዙልሂጃን ጨረቃ በተመለከታችሁ ጊዜ" በሌላ ቃል "አስሩ በገባ ጊዜ" አንድ ሰው ኡዱህያ ማረድ ከፈለገ ከጸጉሩና ከጥፈሩ ይቆጠብ"** *(ሙስሊም፡ 1977)*

በሌላ ቃል **"ኡዱህያን አስከሚያርድ ድረስ ከጸጉሩም ፣ ከጥፍሩም የሆነ ነገር አንዳይቆርጥ"** በሌላ ቃል **"ከአካሉም ይሁን ከጸጉሩ አንድም አንዳይነካ"** *(አህመድ፡ 3149)*

በአስሩ የዙል ሂጃ ቀናቶች መካከል ላይ ኡዱህያ ለማረድ ቢነያ ከነያበት ሰዓት ጀምሮ ጥፍሩንም ይሁን ጸጉሩን እንዳይቆርጥ። ከዚያም በፊት በቆረጠው ሐጢያት የለበትም።

የዚህ ክልከላ ዋናው አላማ በሀጅ ላይ ካሉ ሙእሚን ወንድሞቹ ጋር በተወሰኑ ስራዎች ለማጋራት ነው። ለምሳሌ እነርሱ በሀድይ ወደአላህ እንደሚቃረቡ እርሱም በኡዱህያ ወደአላህ ይቃረባል። ሐጅ ላይ ያሉ ሰዎች ጸጉራቸውን ፣ ጥፍራቸውን ከመቁረጥ ሲከለከሉ ኡዱህያ የሚያርደውም ሰው ከነዚህ ነገሮች ተቆጥቦ ይቆያል ማለት ነው።

ይህ ብይን የሚታረድለት አካል የማይመለከት ፣ በሚያርዱ ሰዎች ብቻ የተገደበ ነው።

ምክንያቱም ነብዩ ﷺ **"ከመካከላችሁ ኡዱሀያ ከማረድ ያሰበ ሰው"** በማለት ነው የሚያርዱ ሰዎችን ብቻ ለይተው የተናገሩት። ረሡል ﷺ ስለቤተሰባቸው ሲያርዱ ቤተሰቦቻቸው ጥፍራቸውንም ይሁን ጸጉራቸውን ከመቁረጥ ይከለከሉ ነበር የሚል አልተገኘም።

በዚህ መሰረት ኡዱሁያ የሚያርደው ሰው ሲቀር ቤተሰቦቹ በአስሩ ቀናቶች ጸጉርና ጥፍር ሊቆርጡ ይችላሉ።

ኡዱህያ የሚያርድ ሰው ከጸጉሩ ፣ ከጥፍሩ ከአካሉ ከቆረጠ ወደአላህ ተጸጽቶ መመለስ እንጅ በሸሪዓ የተደነገገ ቅጣት የለበትም። ይህ ተግባሩ አንዳንድ ጃሂል ሰዎች እንደሚገምቱት ሳይሆን እርድ ከማረድ የሚከለክለው አንዳችም ነገር የለም። ረስቶ ወይም ጃሂል ሆኖ ጸጉሩን ወይም ጥፍሩን ቢቆርጥ ሐጢያት የለበትም። ጥፍሩ አድጎ በጣም ቢቸገር ወይም ጸጉሩ ረዝሞ አይኑ ውስጥ እየገባ ቢያስቸግረውና ጸጉሩን ቢያሳጥረው ሐጢያት የለበትም።

ክፍል ስምንት

እርድ እና መስፈርቶቹ

"ዘካት" ወይም እርድ፥ በነህር ፣ በዘብህ ወይም በጀርህ አማካኝነት የተፈቀዱ እንስሳዎችን ሀላል ማድረግ ነው።

"ነህር" የሚባለው የግመል እርድ ነው። "ዘብህ" የሚባለው ደግሞ ለሌሎች የቤት እንስሳቶች ነው። "ጀርህ" (ማቁሰል) የሚባለው ደግሞ ከአቅም በላይ ለሆኑ እንስሳቶች ነው።

ለእርድ ዘጠኝ መስፈርቶች አሉ፥-

1. **የሚያርደው ሰው ዓቅለኛ እና ነገሮችን የመለየት አቅም ያለው (ተምይዝ) መሆን አለበት። እብድ ወይም ሰካራም ወይም ህጻን መሆን የለበትም።**
2. **የሚያርደው ሙስሊም ወይም የመጽሐፍ ባለቤት - አይሁድ ወይም ነሷራ - መሆን አለበት። ሙስሊም ከሆነ የሚያርደው የተፈቀደ ነው። ወንድም ይሁን ሴት ፣ ፍትሃዊም ይሁን አመጸኛ ፤ ውዱእ የፈታም ይሁን ውዱዕ ያለው እርዱ የተፈቀደ ነው። አባቱ የመጽሐፍ ባለቤትም ይሁን አይሁን የመጽሐፍ ባለቤት ከሆነ እርዱ የተፈቀደ ለመሆኑ ሙስሊሞች ተስማምተዋል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፥-

﴿وَطَعَامُ الَّذِينَ أُوتُواْ الْكِتَابَ حِلٌّ لَّكُمْ﴾

"የአነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው።" *(አል' ማኢዳ፡ 5)*

ነብዩ ﷺ ከአይሁድ በስጦታ የመጣላቸውን የፍየል ስጋ በልተዋል።

ከመጽሐፍ ባለቤቶች ውጭ ያሉ ካፊሮች ያረዱት አይበቃም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَطَعَامُ الَّذِينَ أُوتُواْ الْكِتَابَ حِلٌّ لَّكُمْ﴾

"የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ከእናንተ የተፈቀደ ነው።" *(አል'ማኢዳህ፡ 5)*

ኢማም አህመድ - ረሂመሁሏህ - **"የቢድዓ ሰው ካልሆነ በቀር በዚህ ተቃራኒ የተናገረ አላውቅም"** በማለት ተናግረዋል። ኻዚን በተፍሲር ኪታቡ **"ይህ ጉዳይ ኢጅማዕ ነው"** በማለት ተናግሯል። በዚህ መሰረት ሶሻሊስቶች ኮሚኒስቶች ያረዱት አይበቃም። ሽርካቸው በተግባር የሆኑ ለምሳሌ፡- ለጣዖት የሚሰግዱ ወይም ሽርካቸው በንግግር የሆኑ ለምሳሌ ከአላህ ውጭ የሚጣሩ እርዳቸው የተፈቀደ አይደለም። ሶላት (ሙሉ በሙሉ) የተወ ሰው በአመዛኙ የዑለሞች ንግግር ያረደው አይበቃም። ምክንያቱም ሶላት የማይሰግድ ሰው ካፊር ነው። ገና አዲስ ሰለምቴ ሆኖ ምንም እውቀት ከሌለው በቀር የአምስት ወቅት ሶላትን (መደንገጉን) ያስተባበለም እንዲሁ ቢሰግድም ካፊር ነው። እርሱ ያረደው የተፈቀደ አይደለም።

አንድ ሙስሊም ወይም የመጽሐፍ ባለቤት የሆነ ሰው እንዴት እንዳረደው ወይም ቢስሚላህ ብሏል ወይስ አላለም እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ አይፈቀድም። ይህ በዲን ላይ ጽንፈኝነት ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ አይሁድ ያረደውን በልተዋል፣ ነገር ግን አልጠየቁም።

ቡኻሪ በዘገቡት ትክክለኛ ሐዲስ ዓኢሻ ﵂ የሚከተለውን አስተላልፋለች፡-

ሰዎች ለነብዩ ﷺ *"ሰዎች ሰጋ ይዘው ይመጣሉ ፣ የአላህን ሰም ያውሱ አያውሱ*

አናውቅም" ረሡልም *"ቢስሚካህ ብካችሁ ብኩ"* በማለት መልስ ሰጡ። *(ቡኻሪ፡ 5507)*

ዓኢሻ ﵂ አሁንም የሚከተለውን ተናግራለች - *"እነዚህ ሰዎች በቅርብ የሰለሙ ናቸው ፤ ከመሆኑ ጋር ሳይጠይቁ እንዲበሉ ትዕዛዝ አስተላለፉ።"*

3. ዕርድ መነየት አለበት። አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናገሯል *"ያረዳችሁት ሲቀር"* *(አል'ማኢዳህ፡ 3)*

እርድ ኒያ የሚያስፈልገው ልዩ የሆነ ተግባር ነው። ለምሳሌ የሆነ እንስሳት በላዩ ላይ ሲወጣ ነፍሱን ለማዳን ሲል አርዶ ገደለው። የታረደው ሀላል አይሆንም ምክንያቱም ኒያ የለውም።

4. እርዱ ከአላህ ውጭ መሆን የለበትም። ለምሳሌ ፡ ለጣዖት ልቅና ወይም ለቀብር ባለቤት ወይም ለንጉስ ወይም ለወላጅ ወይም ለመሳሰሉ ነገሮች ልቅና እንዲሁም ኒያ የታረደ መሆን የለበትም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿حُرِّمَتْ عَلَيْكُمُ الْمَيْتَةُ.....وَمَا ذُبِحَ عَلَى النُّصُبِ﴾

(በኽት ... ከጣዖታትም የታረደው እርም ተደረገ) *(አለ'ማኢዳ ፡ 3)*

5. ከአላህ ውጭ የሆነ ስም የተጠራበት ላይሆን ነው። ለምሳሌ፡ የነብዩ ﷺ ወይም የጅብሪል ስም ላይጠራበት ነው። ከአላህ ስም ጋር ከአላህ ውጭ የሆነ ስም ከተጠራበት የተፈቀደ አይሆንም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿حُرِّمَتْ عَلَيْكُمُ الْمَيْتَةُ..... وَمَا أُهِلَّ لِغَيْرِ اللهِ بِهِ﴾

(በኽት ... ከአላህ (ስም) ሌላ የተነሳበትም እርም ተደረገ) *(አል'ማኢዳህ፡ 3)*

በሐዲስ አልቁድስ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"من عمل عملا أشرك فيه معي غيري تركته وشركه"

“ስራን የሰራ ሰው (በዚያ ስራ ውስጥ) ከእኛ ጋር ሌላን አጋርቶ እርሱንም እስከሸርኩ እተወዋለሁ።” (ሙስሊም፡ 2985)

1. በእርሷ ላይ የአላህን ስም ማውሳት ነው። ሲያርዳት “ቢስሚላህ” ሊል ነው።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَكُلُواْ مِمَّا ذُكِرَ اسْمُ اللّهِ عَلَيْهِ إِن كُنتُمْ بِآيَاتِهِ مُؤْمِنِينَ﴾

“በአንቀጾቹም አማኞች እንደሆናችሁ (ሲታረድ) የአላህን ስም በእርሱ ላይ ከተወሳበት እንስሳ ብሉ።” (አል’አንዓም፡ 118)

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"ما أنهار الدم وذكر اسم الله عليه فكلوا"

“ደምን ያፈሰሰ የአላህን ስም ያወሳ በእርሱ ላይ ብሉ” (ቡኻሪ፡ 2488, ሙስሊም፡ 1968)

የአላህን ስም ካላወሳ እርዱ የተፈቀደ አይሆንም።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلاَ تَأْكُلُواْ مِمَّا لَمْ يُذْكَرِ اسْمُ اللّهِ عَلَيْهِ﴾

“በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ።” (አል’አንዓም፡ 121)

አንቀጹ ሁሉንም የሚጠቁም በመሆኑ እያወቀም ይሁን ረስቶ ወይም በማይህምነት የአላህን ስም ካልጠራ ልዩነት የለውም።

ቢስሚላህ ማለት እርድን ሀላል ለማድረግ ነብዩ ﷺ መስፈርት አድርገዋል። መስፈርት ደግሞ በርሳቻና በማህይምነት ውድቅ አይሆንም።

የሚያርደው ሰው ቢስሚላህን መናገር የማይችል ተብታባ ከሆነ በጥቅማ ቢያርድ

እርዱ የተፈቀደ ይሆናል።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَاتَّقُوا اللَّهَ مَا اسْتَطَعْتُمْ﴾

"አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት" *(አት'ተጋቡን፡ 16)*

7. ስለት በሆነና ከብረት ወይም ከዲንጋይ ወይም ከብርጭቆ የተዘጋጀ ቢላዋ መታረድ አለበት።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"ما أنهار الدم وذكر اسم الله عليه فكلوا ما لم يكن سنا أو ظفرا، وسأحدثكم عن ذلك أما السن فعظم، وأما الظفر فمدى الحبشة"

"ደምን ያፈሰሰ በእርሱ ላይ የአላህን ስም ያወሳ ጥርስ ወይም ጥፍር አስካልሆነ ድረስ ብሉ ፤ ስለዚህ ጉዳይ አነግራችኋለሁ ። ጥርስ አጥንት ነው። ጥፍር ደግሞ የሀበሾች ቢላዋ ነው።" *(ቡኻሪ፡ 2488, ሙስሊም፡ 1968)*

ቡኻሪና ሙስሊም ላይ በተዘገበ ሐዲስ ከከዕብ ኢብን ማሊክ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡-

በተራራው ሸለቆ አንዲት ሴት ፍየል እየጠበቀች ከበጎች መንጋ አንዲት ፍየል ጣረ ሞት ላይ እያለች ተመለከተች። ወዲያውኑ ዲንጋይ ሰበረችና አረደቻት። ሶሃቦች ይህን ድርጊቷን ለነብዩ ﷺ ነገሯቸው። እርሳቸውም እንዲበላ አዘዙ።

ባልተሳለ ቢላዋ ለምሳሌ ፡ በማነቅ ፣ በኤሌክትሪክ እና በመሳሰሉት መንገዶች ሩህ ከወጣ አይበቃም። ነገር ግን በዚህ መልኩ ተፈጽሞ ሊያቆያት የሚችል ህይዎት እያላት በሸሪዓዊ እርድ ብትታረድ እርዱ የተፈቀደ ይሆናል።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالْمُنْخَنِقَةُ وَالْمَوْقُوذَةُ وَالْمُتَرَدِّيَةُ وَالنَّطِيحَةُ وَمَا أَكَلَ السَّبُعُ إِلاَّ مَا ذَكَّيْتُمْ﴾

"የታነቀችም ፣ ተደብድባ የተገደለችም ፣ ተንከባካ የሞተችም ፣ በቀንድ ተወግታ የሞተችም ከእርሷ አውሬ የበላካትም (ከእነዚህ በህይወት ደርሳችሁ) ያረዳችሁት ብቻ ሲቀር ..." *(አል' ማኢዳህ: 3)*

ለእንስሳቷ ቀጣይነት ያለው ህይዎት ሁለት ምልክቶች አሉት

አንደኛው፡- መንቀሳቀሷ ነው

ሁለተኛው፡- ደሟ በሐይል መፍሰሱ ነው

8. ደም መፍሰስ አለበት። ማለትም ቢላዋው ሲንቀሳቀስ ደሙ መፍሰሱ መረጋገጥ አለበት።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"ما أنهار الدم وذكر اسم الله عليه فكلوا"

"ደምን ያፈሰሰ በእርሱ ላይ የአላህን ስም ያወሳ ብኩ" *(ቡኻሪ: 2488, ሙስሊም: 1968)*

አመጸኛ እንስሳት ከሆነ ጉድጓድም ይሁን ውሃ ቢገባ ከማንኛውም አካሉ ላይ ደም መፍሰሱ በቂ ነው። በላጩ ግን ሩሁን በፍጥነት ሊያወጣው በሚችለው ነገር ቢሆን መልካም ነው። ምክንያቱም እንስሳቱን ያሳርፈዋል ስቃዩም ይቀላል።

እንስሳቱ በቀላሉ የሚታረድ አይነት ከሆነ የግድ ከአንገቱ በታች ጀምሮ እስከ ሁለት አገጩ ድረስ በጉሮሮ የተከበበውን ሁለቱን ጋኖች እንዲሁም የእርሱን ማሚያ የሆነው ጉሮሮ በመቁረጥ ደም ማፍሰስ ነው። (ሁልቁም) ማለት የትንፋሽ ትቦ ነው። (መሪእ) ደግሞ የምግብና የመጠጥ ትቦ ነው። የእነዚህ ሁለት ትቦዎች መቆረጥ የእንስሳውን ህይዎት በቀላሉ ለማሳለፍ አስፈላጊ ናቸው። በመቆረጣቸውም እርዱ የተፈቀደ ይሆናል።

9. ዕርዱ በሸሪዓ የተፈቀደ መሆን አለበት።

ያልተፈቀደ ከሆነው ሁለት አይነት ነው።

አንደኛው፡- ለአላህ ሐቅ ሲባል እርም የተደረገ። እርሱም፡ የሀረምና የኢሀራምን አውሬዎች አድኖ ማረድ የተፈቀደ አይደለም።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أُحِلَّتْ لَكُم بَهِيمَةُ الأَنْعَامِ إِلاَّ مَا يُتْلَى عَلَيْكُمْ غَيْرَ مُحِلِّي الصَّيْدِ وَأَنتُمْ حُرُمٌ﴾

"በእናንተ ላይ የሚነበበው ብቻ ሲቀር ። የማመክ ፣ የከብት ፣ የበግና የፍየል እንስሳዎች እናንተ በሀጅ ስራ ላይ ሆናችሁ ማደንን የተፈቀደ ሳታደርጉ ከእናንተ ተፈቀዱ።" *(አል'ማኢዳህ፡ 1)*

﴿أُحِلَّ لَكُمْ صَيْدُ الْبَحْرِ وَطَعَامُهُ مَتَاعًا لَّكُمْ وَلِلسَّيَّارَةِ وَحُرِّمَ عَلَيْكُمْ صَيْدُ الْبَرِّ مَا دُمْتُمْ حُرُمًا﴾

"የባህር ታዳኝና ምግቡ ከእናንተም ከመንገደኞችም መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ ከናንተ ተፈቀደ። በሀጅም ላይ እስካችን ድረስ የየብስ አውሬ በናንተ ላይ እርም ተደረገ።" *(አል'ማኢዳህ፡ 96)*

ሁለተኛው፡- ለፍጡር ሀቅ ሲባል የተከለከለ ነው። ተዘርፎ ወይም ተሰርቆ የታረደ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። በዚህ አይነት መልኩ የታረደው ሀላል ነው ወይስ ሀራም በሚለው ዙሪያ ላይ የእውቀት ባቤቶች ልዩነት አላቸው።

ክፍል ዘጠኝ
የእርድ አዳቦች

እርድ የራሱ የሆነ አዳቦች ወይም ስርዓቶች አሉት። ይህ ሲባል ለሀላልነቱ ሸርጥ (መስፈርት) አይደለም። እነዚህ አዳቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በእርድ ጊዜ ወደቂብላ አቅጣጫ መዞር፤
2. በእርድ ጊዜ ለእንስሳዋ መልካም መሆን ። በስለት ቢላዋ ፣ በፍጥነት እና በሀይል ማረድ ነው። አንዳንዶች የሚከተለውን ሐዲስ መረጃ በማድረግ ይህ ግዴታ ከሆኑ አዳቦች ናቸው የሚሉ አሉ።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"إن الله كتب الإحسنان على كل شيء فإذا قتلتم فأحسنوا القتلة وإذا ذبحتم فأحسنوا الذبحة وليحد أحدكم شفرته وليرح ذبيحته"

"አላህ መልካምን ጽፏል ፣ በማንኛውም ነገር ላይ በገደላችሁ ጊዜ መግደልን አሳምሩ ፤ ባረዳችሁ ጊዜ ማረዳችሁን አሳምሩ ፤ አንዳችሁ ቢላዋውን ይሳል ፣ የሚታረደውን ያሳርፍ።" *(ሙስሊም፡ 1955)*

1. በግመል ከሆነ እርዱ "ነህር" መሆን አለበት። በሌላው እንስሳት ላይ ከሆነ ደግሞ "ዘብህ" ይሆናል። የግመል ነህር የግራ እግሯ ተኮልትፎ በሶስት እግሯ ቆማ ትታረዳለች። ይህ ካስቸገረ ተንበርክካ ትታረዳለች። ሌላ እንስሳት ከሆነ ደግሞ በግራ ጎን ተጋድማ ትታረዳለች። ለእርሱ እንዲመች እግሩን ከአንገት ላይ ማኖር ሱና ነው። በእርሷ ላይ በጉልበት መንበርከኩ እና እግሮቿን መያዙ ከሱና መሰረት የለውም። እግሮቿን አለመያዝ ደም በደንብ ለመፍሰስና ለመወራጨት እንዲሁም እንስሳቷ ቶሎ ነፍሷ እንዲወጣ ያግዛል።

2. ከሁለቱ ወፍራም ጋኖች ጋር ሁልቁም እና መሪእን መቁረጥ፤


3. በእርድ ጊዜ ካልሆነ በቀር ቢላዋውን እንስሳቷ መመልከት የለባትም፤

4. "ቢስሚላህ" ከሚለው በተጨማሪ "አሏሁ አክበር" ማለት፤

5. የኡዱህያ ወይም የአቂቃ እርድ ጊዜ "ከቢስሚላህ እና ተክቢራ" ተጨማሪ አላህ እንዲቀበለው የሚከተለውን ዱዓ ማድረግ፡-

"ቢስሚላህ አሏሁምመ ሚንከ ወለከ" ይበል የእርሱ ከሆነ "አኒ" የሌላ ከሆነ ደግሞ ስም ጠርቶ "ሚን ፉላን" ይበል።

وصلى الله وسلم وبارك وأنعم على عبد الله ورسوله نبينا محمد وآله وصحبه أجمعين



ባህር ዳር በሚገኙ የአህሉሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ



http://t.me/alateriqilhaq